# <u>ቃልም ፖለቲካ ነው</u>

ዘወንጌል አዲሱ

በመጀመሪያ ቃል ነበር ተብሏል። ቃል ደግሞ ክቡር ነው የሚባለውን ብዙ ሰው ቢረሳውም ሚዛን ያለው ነው። በፖለቲካ መስክ ቃላት ትርጉምና ሚዛን አላቸው። ስድብ የሚመስላቸው ሰዎች የሚስቱት ይህን ነው። በርግጥ ተሳዳቢዎች አሉ ግን ስያሜዎች በፖለቲካው መስክ ተራ ስድብ ሳይሆኑ መልዕክትና መሰረት ያላቸው ናቸው።

1. ለምን ወያኔ ይባላሉ? በመጀመሪያ ደረጃ ስማቸው ይህ ነው። ጋዜጣቸው ራሱ ወይን ነው የሚባለው። ምግባሪ ክፉ ናቸውና ስማቸው ርግማን ሆነ። ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ የግንጠላ አቀን ቃኝና ፀረ ኢትዮጵያ ነበረ። መለስ ዜናዊ ለስልጣን ሲበቃ አይደለም ወያኔ የተበላሸው። ገና ሲመሰረት ነው። ስለዚህ ውሾን ውሾ ማለት ተገቢ ነው።

2. ለምን ኢሕአዴግ አንለውም? ወያኔ ራሱን ኢሕአዴግ ያለው ጠባብ የትግራይ ድርጅት ሳልሆን ሰፊ ኢትዮጵያዊ የደርጅቶች ስብስብ ነኝ ለማለት ነው። ኢሕአዴግ የተባለው ስም ጨምበል ነው። ወያኔ ኢትዮጵያዊም፤ ዴሞክራሲያዊም፤ አብዮታዊም አይደለም/አልነበረም። በኢሕአዴግ ሽፋን የሰበሰባቸው የጦር እስረኞችና ሕዝብን የከዱ የነበረከት ስምዖን ዓይነቶቹን ነው። በዚህ ሽፋን በመጠቀም ጠባብነቱን የሚያጋልጡትን ሀሰት ብሎ፤ የሚደናገሩትን አደናግሮ ለሰልጣን በቃ። ወያኔ ወያኔ እንጂ ኢሕአዴግ ተብሎ የሚጠራ አይደለም።

3. ህወሓት ኢሕአዴግ በሉት የሚሉ እነማን ናቸው? እነ መለስ ዜናዊ ራሳቸው በዚህ መልክ ሊጠሩና ጠባብና ጎጠኛ፤ዋናውና ብቸኛው ባለስልጣን መሆናቸውን ሊሸፍኑ ይፈልጋሉ። የወያኔ ደርጅት የተባለሸው ከውልደቱ ሳይሆን መለስ አለቃ ከሆነ በኋላ ነው ማለት የሚፈልጉም ኢሕአዴግ ወይም የመለስ ዜናዊ ቡድን መባሉን ይመርጣሉ። ለመለስ ቡድን ያደሩ ወይም ሊያድሩ የሚፈልጉትም ህወሓት/ኢሕአዴግ ማለቱን ይፈልጋሉ---ያስደሰቱ መስሏቸው።

4. ወያኔን ለምን የኢትዮጵያ መንግስት አንለውም? የኢትዮጵያ መንግስት ስላልሆነ ነዋ! የወንበዴ ቡድን ወይም በሕዝብ ላይ የተጫነ አገዛዝ ነው እንጂ መንግስትም የኢትዮጵያም አይደለም። የመለስን አገዛዝ የኢትዮጵያ መንግስት የሚሉ በስህተት እስካልሆነ ድረስ ለወያኔ ያደሩና ለማደር የተዘጋጁት ብቻ ናቸው። የወያኔ ኤምባሲዎችም የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አይደሉም። የመለስም የድርጅት ጦር እንዲሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦር አይደለም።

5. መለስ ዜናዊን ለምን አንቱ አንለውም? አንቱ የሚያሰኝ ዕድሜም ስነ ምግባርም የሌለው ሀገር አጥፊ፤ወራዳም፤ቀጣፊም፤ቅሌታምም ግለሰብ ስለሆነ።

6. ድርጅቶችን ለማፍረስ የተንቀሳቀሱት ለምን አንጃ ይባላሉ? ስራቸው የአንጃ በመሆኑ። አንጃ የተባሉት በስራቸው ነው። በድርጅት ውስጥ ሌላ ድርጅት ለማደራጀት ስለሰሩ። ድርጅቶችን ለማፍረስ ስለተነሱና ስለሚሰሩ። አንጃ ማለት ከድርጅቱ ህግና ደንብ በተፃረረና አብዛኛው ም ጊዜ ምስጢረኛ በሆነ መንገድ በውስጥ ውስጥ ተደራጅቶ ድርጅትን በይፋ የሚያፈርስ ወይም ሊያፈርስ የሚነሳ (ፋክሽን) ማለት ነው። ዶክተር ብርሃኑና አቶ መርሻ አንጃ የሚባሉት በዚህ የተነሳ ነው ። ዶክተር ብርሃኑ ለሁለተኛ ጊዜ አንጃ ሲሆን ነው።

7. ጎጠኛ፣ጎሰኛ፣ ዘረኛ ለምን ይባላል? በመሰረቱ ጠባብ ብሄረተኛ ወይም በብሄረሰብ ደረጃ ልዩነት የሚያደርግ የለየለት ወያኔና መሰሎቹ ለማለት ነው።

8. ወያኔ የትግሬ መንግስት ነውን? የመለስን አገዛዝ የትግሬ መንግስት የማንለው ምንም እንኳን ለክልል አንድ የቆምኩ ነኝ ቢልም የተወሰኑ የገዢው ክፍል አባላትና ካድሬዎቹ ቢጠቀሙ እንጂ፣ ፎቅ ተሰራ አልተሰራ ወዘተ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ በወያኔ አገዛዝ ተጠቃሚ አይደለም። ወያኔ ድሮ የአማራው ሕዝብ ጠላት ነው፣ መንግስት የአማራ ነው፣ አማራው እየተጠቀመ ነውና “ ትግላችን ፀረ አማራ ” ነው ሲል የነበረ ቢሆንም በአፀፋው ወያኔን የትግራይ መንግስት ማለቱ ትክክል አይሆንም። የመለስ ዜናዊ ቡድን የትግራይን ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ለመጋጨትና ለመነጠል ሁሌም እየጣረ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ለትግራይ ጠቀምኩ ብሎም የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንዳሉም የሚካድ አይደለም። የመለስ አገዛዝ የትግራይ ነው ብለው የሚያምኑ የትግራይ ምሁሮችና ተወላጆች እንዳሉም ታይቷል። ተቃዋሚ የተባሉትም የትግራይ ተወላጆች የወያኔ አገዛዝ ሊወድቅ ሲል ከመለስ ባልተናነሰ ተደናግጠው ነበር። ይህ ሁሉ ሀቅ ነው። ግን አገዛዙ የመለስ ቡድንና የጭፍሮቹ እንጂ የትግራይ ሕዝብ ነው ማለት ስህተት ነው።

9. ሁለገብ ትግል ምን ማለት ነው? ይህ በኢሕአፓ በመጀመሪያ የቀረበ አገላለፅ ሲሆን እንደ ሁኔታውና ሚዛኑ ሕዝባዊ አመፅንና ትጥቅ ትግልን አቀናጅቶና አዋህዶ ትግልን ማካሄድ ማለት ነው። ዛሬ የእነ ዶክተር ብርሃኑ አንጃ ይህን አባባል ሊነጥቅና ሊያመክነው መነሳቱ ደግሞ ለሁሉ ም ግልፅ መሆን አለበት።

10. አድርባይ፣ ባንዳና ሆዳም ማለቱ ስድብ ነው ወይ? አይደለም።አድርባይ ማለት መርሁን ሽጦ ወይም መርህ አልባ ሆኖ ለገዢው ክፍል ወይም ለባዕድ የሚያድር ማለት ነው። ሆዳም የሚባለው ደግሞ ለሆዱ አድሮ ሀገርና ወገኑን የሚሸጥ ነው። ስለዚህም አድርባይና ሆዳምን በስሙ መጥራት ስድብ አይደለም። ባንዳ ደግሞ ሀገርና ሕዝብን የሸጠ ነበርና ዘመናዊ ከሀዲዎችን ባንዳ ማለቱ ተገቢና አስፈላጊም ነው።

11.በፖለቲካው መስክ ቦዘኔ ማነው? የፖለቲካ ቦዘኔ ወያኔ ነው፡፡
12. ወያኔን አረመኔና ፀረ ሕዝብ ማለት ይገባል? ሲያንስ ነው፡፡

በፖለቲካው መስክ ቃል በዘፈቀደ የሚወረወር አይደለም ወይም ሊሆን አይገባውም፡፡ ቃላት የፖለቲካ ይዘትንና ጠባይን መሰረት አድርገው ያለውን ገላጭ ናቸው፡፡ ወያኔም አንጃውም ተሰደብን ሲሉ ለምን ማንነታችን ተገለፀ ፤ታወቀ ፤ተጋለጠ በሚል ነው፡፡ ስለዚህም ውሸን ውሾ ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ የወያኔን አገዛዝ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ቅዕልን መስጠት ለወያኔ መቆም ነው፡፡ ቃል ይስተካከል፡፡ ቃል ይከበር፡፡